# ማስታወሻ፦ ከኢትዮጵያ ጉዞዬ፣

## (ክፍል አንድ)


ከዘለቀ ሀብተየስ (አትላንታ)

zelekehab@yahoo.com


ከአገሬ በወጣሁ ልክ በሶስት አመቴ መመለሴ ነበር። ጊዜው አጭር ቢሆንም ለውጡ ግን (በብዙ መልኩ) እጅግ ከፍተኛ ነው። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው እና በማህበራዊ ጉዳዮች አንጻር ባለፉት ሶስት አመታት ውስጥ የተከሰቱ ለውጦችን እንኳን ሰምቶ አይቶም ማመን ይከብዳል። እስቲ እኔም በተወሰኑ ጉዳዮች ዙሪያ ትንሽ ላጫውታችሁ ብዕሬን አነሳሁ።

- በነጻው ፕሬስ ዙሪያ፣
- የተቃውሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ፣
- ትምህርትን በተመለከተ፣
- ስለ የኑሮ ውድነት፣ ወዘተ በተከታታይ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

## 1. ነፃ ፕሬስ

ምርጫ 97ን ተከተሎ ዋነኞቹ የነፃው ፕሬስ ውጤቶች ከህትመት ውጪ መሆናቸው ይታወቃል። በስፋት ከሚታወቁት ውስጥ ጦቢያ ፣ ኢትዮጵ ፣ ጦማር ፣ አስኳል ፣ አባይ ፣ ምኒልክ ፣ ሞገድ፣ ሰይፈ ነበልባል ፣ ወዘተ የሉም። በዚህም ምክንያት በተለይ በፖለቲካ ጉዳይ ላይ አትኩረው በድፍረት ገዢውን ፓርቲ ይተቹ የነበሩ ጋዜጦች ተዘግተዋል። ከምርጫ 97

በፊት ከነበሩ ጋዜጦች ውስጥ ዛሬም ህትመታችውን የቀጠሉ ታዋቂ የግል (የነፃ ፕሬስ ) ጋዜጦች አዲስ አድማስ ፣ ሪፖርተር (አማርኛና እንግሊዝኛ) እና ፎርቹን (በእግሊዝኛ) ናችው። ሶስቱም ጋዜጦች በይዘትም በአላማም ተመሳሳይ ናቸው። ለገዢው ፓርቲ 'ሂሳዊ' ድጋፍ በመስጠት ይታወቃሉ። በተለይ አዲስ አድማስና ፎርቹን የአድርባይ ጋዜጠኝነት ጠንካራ ምሳሌዎች ናችው። ሪፖርተር ከገዢው ፓርቲ ጋር ያለው ልዩነት "የስጋ ትል፣ የዘመድ ጥል" አይነት ሆኖበት እንጂ አድርባይነት አይደለም የሚሉ ብዙ አሉ። ጋዜጠኛ ተስፋዬ ገ/አብን ጨምሮ።

ከምርጫ 97 ወዲህ ህትመት ከጀመሩት ውስጥ ታዋቂ የሚል ስም ያተረፉት አዲስ ነገር፣ የሳምሶን ማሞ ኢትዬ-ቻናል፣ አውራምባ እና ጉግል ናቸው። እስቲ ስለ እነዚህ አዲሶች ጋዜጦች ትንሽ ላውጋችሁ።

አዲስ ነገር በብዙ ነገር ለየት ያለች ናት። ሰፊ ስርጭት አላት። አብዛኛው 'ኢሊት' ቅዳሜ ዕለት ጧት ቀጠሮው ከአዲስ ነገር ጋር ነው። የጋዜጣዋ የቅጠሎች ብዛትም እንደ አዲስ አድማስ፣ ሪፖርተርና ኢትዮ-ቻናል በዛ ያለ ነው። (አራቱም ጋዜጦች ዋጋቸውም እኩል ነው- 5 ብር ነው)። አዲስ ነገር ዘና ብለው የሚሰሩና የሚጽፉ ጋዜጠኞች እንዳሏት ይዘቷ ያስታውቃል። የጋዜጣዋ ባለቤትና ዋና አዘጋጅ አቢይ ተ/ማርያም ያለፈውን የአሜሪካ ምርጫ በቅርብ ሆኖ እንዲመለከት በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ ተጋብዞ አሜሪካ ሰንብቶ ተመልሷል። ቀደም ባለው ጊዜ ቢሆን አዲስ ነገር የCIA ቅጥረኛ የሚል ስም ማትረፏ አይቀርም ነበር። አንድ የኢትዮጵያን ጉዳይ በንቃት የሚከታተል ጓደኛየን "አዲስ ነገር እንዴት

ናት?" ስል ጠየኩት። "አይ ጥሩ ጋዜጣ ናት ፤ መጪውን ጊዜ አስቀድማ ትነግረናለች" አለኝ። ማለት የፈለገውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥያቄ ማቅረብ ነበረብኝ። "ገዢውን ፓርቲም በድፍረት ትተቻለች አይደል?" በማለት ድጋሚ ጥያቄ አቀረብኩ። "ባለቤቱን የተማመነ በግ ላቱን ደጅ ያሳድራል እንዲሉ ነው" አለኝ። የጠረጠርኩት አልቀረም አልኩ በሆዴ።

አዲስ ነገር ዘና ያለች ጋዜጣ ናት። ከላይ እንዳልኩት ገዢውን ፓርቲም ሆነ ተቃዋሚዎች ላይ የሰላ ሂስ ታቀርባለች። ገዢውን ፓርቲ የምትተቸው ባብዛኛው በሰብዓዊ መብት አያያዝና በመልካም አስተዳደር ጉድለቶች ዙሪያ ነው። ወይም በሌላ አነጋገር በመንግስት ፖሊሲዎች ላይ ሳይሆን በአፈፃፀም ብቃት ማነስና ችግሮች ላይ ነው።

አዲስ ነገር 'ተቃዋሚዎችን' ምድር ላይ ወዳለው ነገር ተመልሱ በማለት አበክራ ትመክራለች። ለምሳሌ ያህል *"ስለ አንድነት ጥቂት እንጨዋወት-በግል"* ብሎ አቢይ ተ/ማርያም (የጋዜጣው አዘጋጅ እና ባለቤት) አንድነት ፓርቲን (በወ/ሪት ብርቱካን የሚመራውን) በተለይ ፕ/ር መስፍን ላይ በማትኮር *"ቀኝ አክራሪ"* ብሎ ይከሳል። የክሱ መነሻ በጽሁፉ መሰረት አንድነት ፓርቲ ኢትዮጵያ "ኔሽን ስቴት ናት" ብሎ መነሳቱን በመቃወም ነው። አቢይ በዚህ ጽሁፉ ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ጐሰኝነትና ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት በእኩል ደረጃ ማደግና መነቃቃት ያለባቸው መሆናቸውን በአጽንኦት ይነግረናል። በመሆኑም እንደ ጻፊው እምነት ኢትዮጵያ ውስጥ ሊመሰረት የሚገባው "ሲቪክ ናሽናሊስት ስቴት" (Civic Nationalist State) ነው ይለናል።

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ስለ ኢትዮጵያ ሲናገሩ በተደጋጋሚ “… ዴሞክራሲያዊ ፖለቲካል ኮሚኒቲ ለመፍጠር …” ማለታቸውን ልብ ይሏል። አሁን በቅርቡ ደግሞ ጋዜጠኛ ተስፋየ ገ/አብ ለአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ በሰጠው ቃለ መጠይቅ “ኢትዮጵያና ኤርትራ ብቻ ሳይሆኑ የአፍሪካ ቀንድ አገራት በሙሉ ወደ አንድነት መምጣት አለባቸው” ሲል ተደምጧል። ተስፋየ ይህቺን ጽሁፍ ከእጄ ሳላወጣት ለሶስተኛ ጊዜ ስለ “ታላቁ ቀንድ” ሲሰብክ ሰማሁት። አቶ ተስፋየን ለምን ይሄ ጉዳይ ቀልቡን እንደሳበ መላምት መደርደር አያዳግትም። ለዛሬ ግን ምነው “ከአቅሜ በላይ የሆነን ነገር ስለተጠየኩ ብቻ አልመልስም” የምትላት ትህትናህ በዚህ ጉዳይ ላይ ተዘነጋችህ? ብየ ልጠይቀው ወደድኩ።

ለነገሩ የአባቶቻቸውን ተስፋና ቃል ክደው ባዕድ መሆንን (ግንጠላን) የመረጡ አያሌ የኤርትራ ልጆችን እናውቃለን እንጂ እንደ ተስፋየ አባቶቻቸው ከኢትዮጵያ መለየትን በደስታ መርጠው ልጆቻቸው “ኢትዮጵያዊ ነኝ” የሚሉ ብዙም ባለማወቃችን በሱ ደስ ይለናል። (በኤርትራው “ውሳኔ-ህዝብ” ወቅት ቢሸፍቱ የነበሩት ወላጆቹ “ያለ ማንም ተጽዕኖ በደስታ ነው ድምጽ የሰጡት” ሲል ለአዲስ-ድምጽ ራዲዮ መናገሩ ይታወቃል - ምርጫው ደግሞ ‘ባርነት’ ወይም ‘ናጽነት’ እንደነበር የሚታወስ ነው።)

በዚህ አጋጣሚ ለአንባቢዎቼ መግለጽ የምፈልገው ‘በአብዮታዊ ዴሞክራሲ፣’ ‘ሲቪክ ናሽናሊስት ስቴት፣’ ‘ፖለቲካል ኮሚኒቲ፣’ ‘ሶስተኛው አማራጭ’ (third way) እና ‘ታላቁ ቀንድ’ (greater horn initiative) መካከል ያለ አንድነትን እና ልዩነትን ዓይናችንን

ገልጠን እንድንከታተልና እንድንመረምር ነው። ቃላትን መመርመር ይኖርብናል፤ "በመጀመሪያ ቃል ነበር …" አይደል ያለው መጽሃፉ። ቃል ይቀድማል የስራ ስጋም የለብሳል።

ወደ ጀመርኩት የጋዜጦች ዳሰሳ ልመለስና ስለ ኢትዮ-ቻናል ትንሽ ነገር ልበል። ትንሽ ማለቴ ጋዜጣዋን እንደ ጋዜጣ፣ አዘጋጆቿንም እንደ ጋዜጠኛ ለማየት ስለምቸገር ነው። 'ጋዜጣዋ' ዋነኛ የዘገባዎቿ አቅጣጫ በሁለትና ሁልት ነገሮች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። የመጀመሪያውና ዋነኛው ተልዕኮዋ ሼኩን ማሞገስና ማወደስ፣ ከየትኛውም አቅጣጫ የሚሰነዘርባቸውን ትንኮሳና ጥቃት መከላከል ነው። ሁለተኛው ተግባሯ አንድነት ፓርቲን መሰለል፣ በፓርቲው ስብሰባ ወቅት ማን ምን እንዳለና የስብሰባውን ቃለ-ጉባዔ በፊት ገጿ ላይ ማተም ነው። እኔም ታድያ ኢትዮጵያ በቆየሁበት ጊዜ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች ጠንከር ባለ ጉዳይ (hot issue) ላይ ስብሰባ እንደተቀመጡ ከሰማሁ በሳምንት ሁለቴ የምትወጣውን ኢትዮ-ቻናልን ጠብቄ ቃለ-ጉባዔውን አነብና ቀድጄ እጥላታለሁ።

በኢትዮ-ቻናልና በአንድነት ፓርቲ ዙሪያ አንድ የሚያስቅም የሚያናድድም ነገር ላጫውታችሁ። የፓርቲውን ምስጢር ማን ለኢትዮ-ቻናል እንደሚያቀብል የሚያጠና እና የሚመረምር ኮሚቴ ፓርቲው በምስጢር አዋቀረ። በነጋታው ኢትዮ-ቻናል የኮሚቴውን አባላት ስም ዝርዝር አስነበበችን።

አውራምባ እና ጉግል ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው ማለትም ከአዲስ አድማስ፣ ከሪፖርተር፣ ከአዲስ ነገር እና ከኢትዮ-ቻናል በይዘት የተለዩ

ናቸው። በገጽ  ብዛትም አነስተኛና ዋጋቸውም 3.50 ብር ነው። ከላይ እንዳልኩት በይዘት ደረጃም በተወሰነ መልኩ ይለያሉ። ለምሳሌ ያህል አገር ቤት "የጋዜጤኛው ማስታወሻ" ስለተሰኘው መጽሀፍ  ሽፋን የሰጠው አውራምባ ጋዜጣ ብቻ ነው። ሌሎች ጋዜጦች ያንን የመሰለ ትኩስና የህዝብን ቀልብ ስለገዛ ጉዳይ በተለይ በፊት ገጻቸው ላይ አንድም ዜና አልሰሩበትም።

ሌላው ከምርጫ 97 ወዲህ በዋናዎቹ ጋዜጦች መዘጋት ምክንያት የ 'ዲያስፖራው' እንቅስቃሴ አገር ቤት የሚሰማበት መንገድ በጣም ጠቧል። ለምሳሌ በG20 አገሮች ስብሰባ ወቅት በአቶ መለስ ላይ ተደርገው የነበሩ የተቃውሞ ሰልፎች በአገር ቤት አልተሰሙም ማለት ይቻላል። ይህን አይነቱን ክፍተት ለመሸፈን ሲሞክሩ የሚታዩት አውራምባ እና ጉግል ናቸው። የሎንደኑን ተቃውሞ ሰልፍ ግን እነ አውራምባም አልዘገቡም። ምክንያታቸውን አላውቅም።

ለአዲስ አድማስና ለሪፖርተር እንዲሁም ለፎርቹን ግን 'ዲያስፖራው' እርባና ቢስ፣ አክራሪ፣ ጨለምተኛ፣ ወዘተ ነው። በመጨረሻም በዳሰሳየ መሰረት አውራምባና ጉግልም ቢሆኑ በጥንካሪያቸው ገፍተው እንደቀድሞዎቹ እንደነ ኢትዮጵ፣ ጦቢያ፣ ጦማር፣ ምኒልክ፣ ወዘተ መስዋትነት ለመክፈል ጭምር ዝግጁነት አላቸው ለማለት በፈልግ ብዕሬን ይይዘዋል።

እናም ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት ነጻ፣ ደፋርና ህዝባዊ ፕሬስ የለም ብሎ መደምደም ይቻላል።

## 2. የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ

አንድ ኢትዮጵያ ደርሶ የተመልሰን ሰው የፖለቲካው ሁኔታ እንዴት ነው ተብሎ ቢጠየቅ ሊሰጥ የሚችለው መልስ እንደየ ሰዉ ሊለያይ መቻሉ እውነት ነው። እኔም ከመሄዴ በፊት ጠይቄ አውቃለሁ። የአብዛኞቹ መልስ ግን ተመሳሳይ ነው። "ምንም የሚታይ ነገር የለም። ሰዉ ተስፋ ቆርጦ ዝም ብሏል" የሚሉ አይነት መላሾች ናቸው የሚያጋጥሙት።

ከምርጫ 97 ወዲህ በተለይ በከተሞች ውስጥ የመንግስት የስለላና የደህንነት መዋቅር በከፍተኛ ደረጃ ጥብቅ ሆኗል። በመሆኑም በመዝናኛ አካባቢዎች፣ በካፍቴሪያዎች ውስጥ፣ በታክሲ እየተጓዙ ወዘተ አብርዎት ካለው ጓደኛዎ ወይም ዘመዶ ጋር ፖለቲካዊ ነገር አንስቶ መጨዋወት የሚያስፈራ ሆኗል። የወያኔ መንግስት ቢያንስ ለወሬ ሰጥቶት የነበረውን ፈቃድ አንስቶታል።

አዲስ አበባ አንድ ነጋዴ ጓደኛ አለኝ። ልጎበኘው ወደ ሱቁ ሄድኩ። ጭማቂ እንጠጣ አለኝና ከሱቁ ወጥተን ባካባቢው ካለ አንድ 'ካፍቴሪያ' ገባን። ቤቷ በደንበኞች ጢም ብላለች። አብዛኞቹ የዕለቱን ጋዜጦች ያነባሉ። ጋዜጣ አንብቦ መግዛት ያልፈለገ ወይም ያልቻላ እዚያው ቁጭ ብሎ ካነበበ (ገረፍ፣ ገረፍ ካደረገ) በኋላ ለጋዜጣ አዟሪው ከ0.50 ሳንቲም እስከ 1 ብር ሰጥቶ ጋዜጣውን መመለስ የተለመደ ነው። ኑሮ በዘዴ ይሏችኋል ይሄ ነው። (ከሶስት አመት በፊት 1 ብር ጋዜጣ መግዣ ዋጋ እንጂ ለአንድ አፍታ ንባብ ኪራይ የሚከፈል አልነበረም።) ጓደኛየ እና

እኔም ጭማቂያችንን አዘን የተለመደ ወጋችንን ልንሰልቅ ጉሮሮውን ጠረግ አድርጎ ሊጀምር አለና በድንገት አቋርጦ ዞር፣ ዞር ብሎ ከጎናችን የተቀመጡትን ቃኘ። ያውቃቸዋል። "እንዲሁ ነው እዚህ የመጣነው፤ ጭማቂውን ሱቅ እንዲያመጡልን እነግራቸዋለሁ " ብሎኝ ተመልሰን ወደ ሱቁ ሄድን።

"ምን ነው? ምን አይተህ ነው?" ስል ጠየቅኩት ወደ 'ወገን ወረዳ' (ሱቅ) እንደደረስንና ጓደኛየ ላንድ አፍታ ተፈጥሮበት የነበረውን የመረበሽ ስሜት በግርምት እያስታወስኩ። "ጁስ ቤቷ ውስጥ ካሉት ግማሽ ያህሉ የወያኔ ደህንነቶች ናቸው" አለኝ። በአጠቃላይ አፈናውም ፍርሃቱም ነግሷል። በዚህ አይነቱ የፖለቲካ ድባብ ውስጥ ነው እንግዲህ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ መቃኘት የሚጠበቅብን።

ባሁኑ ወቅት ባብዛኛው የፖለቲካ 'ኢሊት' መሀከል የመወያያ ርዕስ ከሆኑት የፖለቲካ ሀይሎች ውስጥ ግንባር ቀደሞቹ ግንቦት 7፣ አንድነት፣ መድረክ፣ መኢአድ እና ኦነግ ናቸው። ቀደም ሲል በኢህፓ ደጋፊነት የማውቃቸውም ቢሆኑ ዛሬም እጅ አልሰጡም።

## 2.1 ግንቦት ሰባት፣

(ይቀጥላል)

ቸር እንሰንብት፣
እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ